Español: masspowerchoice.com/cambridge/letter_spanish.pdf
Kreyòl ayisyen: masspowerchoice.com/cambridge/letter_hcreole.pdf
বাংলা: masspowerchoice.com/cambridge/letter_bangla.pdf
አማርኛ: masspowerchoice.com/cambridge/letter_amharic.pdf

# የካምብሪጅ ከተማ

## የማህበረሰብ ኤሌክትሪክ መሰብሰቢያ ፕሮግራም
## የማሳወቂያ ደብዳቤ

ፌብሩዋሪ 12፣ 2018

ውድ የካምብሪጅ ነዋሪ ወይም የንግድ ተቋም

ይህ ደብዳቤ የኤሌክትሪክ ክፍያዎን በተመለከተ ጠቃሚ መረጃ ይዟል።

በአሁኑ ሰአት Eversource መሰረታዊ አገልግሎት አለዎት። ይህ ማለት Eversource የእርስዎን እሌክትሪክ ያደርሳል፣ እንዲሁም Eversource በተጨማሪም የእርስዎ ኤሌክትሪክ አቅራቢ ነው (ለእርስዎ ኤሌክትሪክን ይገዛል)።

ሆኖም ግን የካምብሪጅ (Cambridge) ከተማ የካምብሪጅ የማኅበረሰብ ኤሌክትሪ (Cambridge Community Electricity) የተባለ የኤሌክትሪክ ማጣመር ፕሮግራም አላት። በዚህፕሮግራም ውስጥ፣ ኤቬርሶርስ (Eversource) ለእርስዎ ኤሌክትሪክ ማቅረቡን ይቀጥልበታ፤ ነገር ግን ከተማዋ ለራሷ ኤሌክትሪክ የሚያቀርብላትን የራሷን አቅራቢ መርጣለች። የከተማዋ ኤሌክትሪክ አቅራቢ ኤቬርሶርስ (Eversource) ከሚያቀርበው በላይ በሚውስዱት ኤሌክትሪክ ላይ በርካታ ታዳሽ ኃይልን ይሰጣል። ውድድር ባለው የጨረታ ሂደት ውስጥ፣ ካምብሪጅ (Cambridge) በጁላይ 2017 ላይ ከሚጀምረው፣ ከአጌራ ኢነርጂ (Agera Energy) ጋር የ18 ወራት ኮንትራት ተደራድሯል።

**ተሳታፊ ላለመሆን እስካልመረጡ ድረስ በካምብሪጅ ማህበረሰብ ኤሌክትሪክ ውስጥ በቀጥታ ይካተታሉ። መሳተፍ አያስፈልግም**

ተሳትፎ ማለት: የአጌራ ኤልክትሪክ (Agera Energy) አቅራቢን እና ኤሌክትሪክ በሚያቀርብልዎት የኤቬርሶርስ (Eversource) የኤልክትሪክ ክፍያ ሥር ሆነው የድርሻዎ የዋጋ መርኃግብሩን ያዩታል። ሆኖም ግን፣ የእርስዎ ዋናኛ ኤሌክትሪክ ለማግኘት ግንኙነት የሚያደርጉት ከኤቬርሶርስ (Eversource) ጋር ሆኖ ይቀጥላል።

- ደረሰኝዎ ከ Eversource መምጣቱን ይቀጥላል
- ክፍያዎችን ወደ Eversource መላክዎን ይቀጥላሉ
- መብራት ከተቋረጠብዎ ወደ Eversource መደወልዎን ይቀጥላሉ

**ለዝቅተኛ ገቢ የአቅርቦት ዋጋ ወይም ለነዳጅ ድጋፍ ብቁ ከሆኑ፣ እነዛን ጥቅማጥቅሞች መቀበልዎን ይቀጥላሉ።**

አለመሳተፍን መምረጥ ማለት፡- Eversource የኤሌክትሪክ አቅራቢዎ መሆኑን ይቀጥላል፣ የክፍያዎ የአቅርቦት ክፍል በ Eversource መሰረታዊ አገልግሎት መጠን ይሆናል ማለት ነው፡፡

## የመሳተፍ ጥቅሞች

ቁጠባዎች - የዋጋ መርኃግብሩ በአሁኑ ጊዜ ከኤቬርሶርስ (Eversource) ከመሰረታዊ አገልግሎት ያነሰ ነው። ሆኖም ግን፣ የኤቬርሶርስ (Eversource) መሰረታዊ አገልግሎት ዋጋ ለነዋሪዎች እና ለትንንሽ የንግድ ደንበኞች በየስድስት ወራቱ የሚለወጥ ሲሆን ለመካከለኛ እና ለትላልቅ የንግድ ደንበኞች በየሦስት ወራቱ ይለውጣል። ስለሆነም፣ የዋጋው መርኃግብር ከኤቬርሶርስ (Eversource) መሰረታዊ አገልግሎት ዋጋ በታች ሆኖ ላይቆይ የሚችል ሲሆን፣ ቁጠባዎችም ዋስትና ሊሆን አይችሉም።

የአካባቢ፣ ታዳሽ ኤሌክትሪክ - አሁን የእርስዎ ኤሌክትሪክ በግዛቱ ከሚፈለገው ዝቅተኛ መጠን በላይ የፀሐይ ሃይልን ያካትታል፣ እናም ጭማሪው የፀሐይ ሃይል በካምብሪጅ እና አካባቢው ካሉ ፕሮጀክቶች የሚመጣ ይሆናል።

ምርጫ - መርኃግብሩ ሁለት አማራጮችን ይሰጥዎታል: 1) ደረጃውን የጠበቀ አረንጓዴ (Standard Green)፣ በመንግሥት ከተጠየቀው ከአነስተኛው መጠን በላይ ብዙውን ኃይል ከፀሐይ ብርሃን ማግኘት፣, እና 2) 100% አረንጓዴ (Green)፤ ወዲያውኑ በደረጃውን የጠበቀ አረንጓዴ (Standard Green) በሚለው መርኃግብር ውስጥ ይገባሉ፤ ነገር ግን 100% አረንጓዴ (Green) የሚለውን መምረጥ ይችላሉ። (ዝርዝሩ በጀርባ ላይ ይገኛል)

## ካምብሪጅ
## የማህበረሰብ ኤሌክትሪክ

የአዲሱ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ዋጋ

**10.486 ¢/kWh**

Eversource የመኖሪያ ቤት መሰረታዊ አገልግሎት

**13.157 ¢/kWh**

የ Eversource የንግድ ታሪፎች ጀርባው ላይ። ▶

### የደንበኞች አገልግሎት፡-

**1-888-589-7790**

### ለመሳተፍ አይፈልጉም?

አይኖርብዎትም። ከፕሮግራሙ ለመውጣት ቅጣትም ሆነ ክፍያ የለም፣ እናም በማንኛውም ጊዜ መውጣት ይችላሉ።

ላለመሳተፍ ከመረጡ፣ የ Eversource Basic Service ደንበኛ እንደሆኑ ይቀጥላሉ።

ከመቀላቀልዎ በፊት ለመውጣ ከፈለጉ፤ ከ ማርች 19፤ 2018 በፊት ከሚከተሉት አንዱን ያድርጉ: ምዝገባ - ጃንዋሪ 2019 የሜትር ንባብ፡፡

▶ (ከማርች 19, 2018 በኋላ የማይላከውን) የታሸገውን ካርድ ይፈርሙ እና ይመልሱ፤ ለ Agera Energy በ 1-888-589-7790 ይደውሉ፤ ወይም በድረገፅ www.masspowerchoice.com/cambridge ይውጡ፡፡

ወደፊት እራስዎን ለማስወጣት፣ ከሚከተሉት አንዱን በማንኛውም ጊዜ ያድርጉ፡-

▶ Agera Energyን በዚህ ያናግሩ 1-888-589-7790 ወይም በኢንተርኔት በ www.masspowerchoice.com/cambridge መርጠው ይውጡ።

## የፕሮግራም አማራጮች እና ዋጋ አሰጣጥ

| 1. ምንም ካላደረጉ፣ በቀጥታ በ STANDARD GREEN ይካተታሉ፦ | **10.486 ¢/kWh*** ለመኖሪያ፣ አነስተኝ ንግዶች፣ እና ትላልቅ የንግድ አካውንቶች (ይህ ከሁሉም የሚረክሰው አማራጭ ነው) |
|---|---|
| የታዳሽ ሃይል ይዘቶች | ከፀሐይ የሚገኘውን ኃይል መንግሥት የሚጠይቀውን ከአነስተኛው 2.8628% በግምት ወደ 3.5785% (a 25% በመጨመር) በመጨመር በካምብሪጅ (Cambridge ) ውስጥ ወይም አቅራቢያ የሚመረተውን የፀሐይ ኃይልን መጠቀም። ** |
| የታሪፍ ጊዜ | ምዝገባ - ጃንዋሪ 2019 ሜትር ይነበባል። |
| የመውጫ መመሪያዎች | በፈለጉት ጊዜ ይተዉ። የመውጫ ክፍያ የለም። |

| 2. 100% ታዳሽ ሃይል ከፈለጉ፣ 100% GREEN ሊመርጡ ይችላሉ፦<br>▶ 100% GREEN ለመምረጥ በዚህ Agera Energyን ያናግሩ 1-888-589-7790። | **12.180 ¢/kWh*** ለመኖሪያ፣ አነስተኝ ንግዶች፣ እና ትላልቅ የንግድ አካውንቶች (ይህ ከሁሉም የሚወደደው አማራጭ ነው) |
|---|---|
| የታዳሽ ሃይል ይዘቶች | 100% ንጹህ ሃይል በኒው ኢንግላንድ ካሉ የታዳሽ ሃይል ፕሮጀችቶች። |
| የታሪፍ ጊዜ | ምዝገባ - ጃንዋሪ 2019 ሜትር ይነበባል። |
| የመውጫ መመሪያዎች | በፈለጉት ጊዜ ይተዉ። የመውጫ ክፍያ የለም። |

| 3. ላለመሳተፍ ከመረጡ፣ በ EVERSOURCE BASIC SERVICE ላይ ይቀጥላሉ። | **12.888 ¢/kWh** መኖሪያ<br>**12.692 ¢/kWh** አነስተኛ ንግድ<br>**14.639 ¢/kWh** መካከለኛ እና ትልቅ ንግድ |
|---|---|
| የታዳሽ ሃይል ይዘቶች | የማሳቹሴትስን ዝቅተኛ የታዳሽ ኃይል መስፈርቶች የሚያሟላ። |
| የታሪፍ ጊዜ | ከ ፌብሩዋሪ 1, 2018 - ጁን 30, 2018, ለመኖሪያ እና ለአነስተኛ የንግድ አካዉንቶች፡፡ ከ ፌብሩዋሪ 1, 2018 - ማርች 31, 2018, ለመካከለኛ እና ትላልቅ የንግድ አካውንቶች፡፡ የኤቨርሶርስ ውስን መሰረታዊ የአገልግሎት ታሪፎች ለመኖሪያ እና ለአነስተኛ የንግዶ አካውንቶች በየ 6 ወራት፤ እንዲሁም ለመካከለኛ እና ትላልቅ የንግድ አካውንቶች በየ 3 ወራት ሊቀየሩ ይችላሉ፡፡ |
| የመውጫ መመሪያዎች | በፈለጉት ጊዜ ይተዉ። የመውጫ ክፍያ የለም። |

* የ Standard Green ዋጋ እና የ 100% Green ዋጋ ሁለቱም $0.00075/kWh የአስተዳደር ክፍያን ያካትታሉ።

** የተጨማሪ የ25% የፀሃይ ጉልበት ኃይል ግዢ በክልሉ በ2018 ከሚጠየቀው ዝቅተኛ መስፈርት በተጨማሪ በቀጥተኛነት የሚያመላክተው፤ ከ SREC II-ብቁ የሆኑ ፕሮጀክቶች፤ የማሳቹሴትስ የኃይል ሰርተፊኬት (SRECs) ነው፡፡ ፐርሰንታይሉ የተመሰረተው በኤሌትሪክ የሽያጭ ትንበያ ላይ ነው፡፡

## ተደጋግመው የሚነሱ ጥያቄዎች

ቁጠባዎች እንደ ዋስትና ይሰጣሉ? አይሰጡም። የዋጋው መርኃግብር የአሁኑ የኤቬርሶርስ (Eversource) የዋጋ ስምምነት እስከሚያበቃበት ድረስ ከኤቬርሶርስ (Eversource) ያነሰ መሆኑን ዋስትና ይሰጣል። ቀጥሎ የ Eversource ዋጋ በ ጃኑዋሪ 1፣ 2018 ለመኖርያ ቤቶች እና አነስተኛ ንግድ፣ እንዲሁም ለመለስተኛ እና ታላቅ ንግድ ሂሳቦች በጁላይ 1፣ 2018 እና በኤፕሪል 1፣ 2018 ይለወጣል፡፡ For current rates, አሁን ላለው የዋጋ ሁኔታ ለማየት፣ የሚከተለውን ድኅረገጽ ይጎብኙ። https://www.eversource.com/Content/ema-c/residential/my-account/billing-payment/rates-tariffs/basic-service.

ቀድሞውኑ ከኤሌትሪክ አቅራቢ ጋር የራሴን ውል ፈርሜያለው፡፡ ምን ማድረግ ይገባኛል? ከኤሌትሪክ አቅራቢው ጋር ነባራዊ ውል ካልዎት፤ እናም በዚህ ውል መቆየት የሚፈልጉ ከሆነ፤ ከካምብሪጅ የማሕበረሰብ የኤሌትሪክ ፕሮግራም ውስጥ መውጣት አለብዎት፡፡ ከፕሮግራሙ መውጣት አለመቻል፤ በፕሮግራሙ ውስጥ መመዝገብን እና ከጊዝያዊው የኤሌትሪክ አቅራቢ የቅጣት ክፍያን ሊያከትል ይችላል፡፡

በይዞታዬ ላይ የሶላር ፓነሎች አሉኝ። የተጣራ የቆጣሪ ንባብ ሂሳብ መቀበሌን እቀጥላለሁ? አዎ። ፕሮግራሙ ውስጥ ቢሳተፉም የተጣራ የቆጣሪ ንባብ በተመሳሳይ መንገድ ይሰራል። ከሶላር ፓነሎችዎ የሚመጡት የተጣራ የቆጣሪ ንባብ ሂሳቦች በ Eversource ደረሰኞችዎ ላይ መታየታቸው ይቀጥላሉ እንዲሁም በ Eversource መሰረታዊ አገልግሎት ዋጋ መሰረት መታሰባቸውን ይቀጥላሉ።

ማንኛውም ተጨማሪ ጥያቄዎች ካለዎት፣ የደንበኛ ድጋፍ ክፍልን በ 1-844-379-9934 ወይም በ cambridge@masspowerchoice.com ያግኙ ወይም www.masspowerchoice.com/cambridge ን ይጎብኙ። የፕሮግራም አማካሪዎቻችን እርስዎን ለመርዳት ፍቃደኛ ናቸው።

Louis DePasquale
የከተማው አስተዳዳሪ

# የመውጫ መመለሻ ካርድ

## የካምብሪጅ ማህበረሰብ ኤሌክትሪክ ፕሮግራም

X ______________________________________________

ፊርማ ቀን

### የመውጫ መመሪያዎች

በካምብሪጅ ማህበረሰብ ኤሌክትሪክ ውስጥ ለመሳተፍ ምንም አይነት እርምጃዎችን መውሰድ አይኖርብዎትም።

ለመሳተፍ ካልፈለጉ:-

1. በዚህ ካርድ ላይ ቀኑን ጽፈው ይፈርሙ
2. ካርዱን በተካተተው ፖስታ ያድርጉና ፖስታውን በ ፖስታ ይላኩት።

ይህ ካርድ ስሙ በዚህ ካርድ ላይ በተገለጸው በተመዘጋቢው ደንበኛ መፈረም አለበት። ከመቀላቀልዎ በፊት ለመውጣት ከፈለጉ፤ እሽጉ ለመላክ ከ ማርች 19, 2018 በኋላ ማለፍ የለበትም፡፡ ከተመዘገቡም በኋላም ቢሆን በየትኛውም ጊዜ ምርጫ ማድረግ ይችላሉ።